# ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ።መዝ፤44(45)ቁ1

## “የኔስ ምኞት”

የደከመውን ላበረታ
ያዘነውን ላፅናና
የባከነውን ላረጋጋ
ድፍረትን በትህትና
ጥላቻን በፍቅር
ክፋትን በደግነት
ተንኰልን በየዋህነት
ንፍገትን በቸርነት
ቂም በቀልን በይቅርታ
ማጉረምረምን በምስጋና
ለመተካት በአዲስ ፍሬ
ስሙን ልናገር ላወሳ
ሐሰትን ጥዬ ዕውነትን ላነሳ
ላስታውሰው በህይወት ዘመኔ
የአምላኬን ስም ልጠራ በዝማሬ
ተኩላነቴ ተለውጦ
በግነቴ ተረጋግጦ
ወደ ማደርያው ልገባ
እረኛውን ተማምኜ
አቤት ልለው ስሜን ሲጠራ
የሚያምረው ድምፁ ሲያስተጋባ
ከጉያው ላለመውጣት
ወደ ዱር ላለመግባት
እንዲታደገኝ መድህኔ
እሾህ አሜኬላ ያለበትን
ጠምዛዛ መንገድ ትቼ
እንክርዳዱን ከሚዘራው
ከጠላት ዲያብሎስ ነቃፊው
ርቄ ልሂድ በጠባቡ
ራሴን ልመራ በአግባቡ
ስንፍናን ላሰናብት
ላልጠመድ በአሉባልታ
በወሬ ላልፈታ
አንደበቴን ልገታ
ቦታ ላልሰጥ ለሐሜታ
እጄን ላልጠቁም በሌላው
የራሴን ጉድፍ ላወጣው
ሐይማኖቴን ልጠብቅ
እንዲሆነኝ ለዕምነቴ ስንቅ
ዕውቀትን ለመገብየት
ለሌላው ተርፌ ለመታየት
ከማራኪዋ ዓለም አምልጬ
ጆሮ ዳባ ማለትን ትቼ
ከአባቶቼ እግር ስር ተቀምጬ
ምስጢራትን ሲያራቅቁ
እየገቡ ወደ ጥልቁ
ብሉይና ሐዲስን
አስማምተው ሲያስተምሩ
አትርፌ ልመጣ መክሊቴን
መክሰሴን ልተው ጌታዬን
እንዳልጣል ወደ እሳቱ
ወደ ጥርስ ማፋጨቱ
ነበረ የኔስ ምኞት
ከብዙ በጥቂቱ
ዘግይቼ ለመናገር
ፈጥኜ ለመስማት
መልካም ነገርን በመመኘት።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
ለንደን(ኅዳር፡2002 ዓ/ም)